# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ልዩ ዕትም ሚያዚያ-ግንቦት 2003 ዓ.ም


## <u>የፖለቲካ ድርጅት ለትግል፤ ጽናት ደግሞ ለድል!</u>

(ለኢሕአፓ 39ኛ ምስረታ ዓመት)

የዛሬ 39 ዓመት ኢሕአፓን የመሠረቱት ኢትዮጵያውያን ዋናና መሠረታዊ መነሻቸው በማንኛውም ሚዛን ቢለካ ኋላ ቀር የሆነችውን ሀገራቸውን ለማሳደግና ለማበልጸግ፤ እየተበደለና እየተሰቃየ የሚገኘው የሚወዱት ህዝባቸው በትግላቸው ነፃነቱን እንዲጎናፀፍ ለማድረግና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተሸጋግሮ፤ ሰላምን አግኝቶ፣ እድገትን የተላበሰ ኑሮ የሚመሩበት ሁኔታ እውን እንዲሆን ከነበራቸው ፅኑ ፍላጎት ነበር። ምንም እንኳ ቆርጠው ለተነሱበት ትግል በአርዓያነት የሚመለከቱትና ከአካሄደው ትግልና ካገኘው ተመክሮ ራሳቸውን ለማነጽ የሚችሉበት ቀዳሚ የፖለቲካ ድርጅት ባይኖርም፤ ተመክሮን ለመገብየት የግድ ራሳቸውን ከማንም በበለጠ በትግል እሳት እየፈተኑ መታገልን የግድ ብሏቸዋል። ይህ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲ ለመሆን የበቃውና የበኩር ልጅ የተሰኘውን ስም ለመጎናፀፍ የቻለውን ኢሕአፓ የመሰረቱት፣ በለጋ ወጣትነታቸው ለትግል ሲነሱ፣ በሥልጣን ላይ የነበረው አገዛዝና ሥርዓቱ በጣም ኋላቀርና ለለውጥም እንቅፋት ነበር። ለብዙሃኑ እድገትና ብልጽግና ለማስገኘት ሥርዓቱን ከሥር-መሠረቱ ፈንግሎ መጣል አስፈላጊ መሆኑን ያመኑና የተገነዘቡ ወጣቶችን በማሰባሰብ ኢሕአፓ ተምጦ እንዲወለድ ማድረግ ወቅቱ ግዴታ ያለውም በዚሁ ምክንያት ነበር። ኢሕአፓም ጉዞዉን ያለ ሕዝብ አመኔታና ተሳትፎ ትርጉም የለሽነቱን ገና ከመነሻው ነበር ያስቀመጠው። ይህንኑ በውል በማጤን በትግሉ ሠራተኛውን፣ ገበሬውን፣ ምሁሩን፣ ወጣቱን፣ ሴቶችን፣ ጭቁን ወታደሩን፣ …ወዘተ ማነሳሳትና ለችግሮቻቸውም አብሮ መፍትሄ መፈለግ እንዳለበትም ከመጀመሪያው ተረድቷል።

በርግጥም ዛሬ ወደኋላ መለስ ብለን ያለፈውን የ39 አመት የትግል ታሪክ በሕሊናችን ስንቃኝ፣ ይህ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝብ የበኩር ልጅ ኢሕአፓ፣ ከሕዝቡ ጋር በመሆን ሊያስወግዳቸው የታገለላቸው ዋና ዋና ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲሁም ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለምንም ገደብ ይከበሩ የሚሉት እንደነበሩ እንረዳለን። ዘርዘር አርገን ይህንን ስናየው፣ መብት ለአርሶ አደሩ፣ ለላብ አደሩና ለከተሜው ሠርቶ አደር፣ ለሴቶች፣ ለብሔር/ብሔረሰቦች፣ የሚሉትን ይጠቀልላል። መሬት ላራሹ እንዲሆን፤ ዴሞክራሲ ለሕዝብ እንዲሰፍን፤ የሀገር ሉዓላዊነት እንዲጠበቅ፤ የዜጎች አንድነት በእኩልነት እንዲረጋገጥ፤ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ለብዙሃኑ እንዲዳረስ፤ ሀገር የጋራ ሃይማኖት የግል በሚለው መርህ መሠረት የእምነት እኩልነት ተረጋግጦ መንግሥትና ሃይማኖት ለየቅል እንዲሆኑ፣ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲፈታ፤ የንግግር፤ የጽሁፍና የመደራጀት መብቶች እንዲከበሩ፤ ለሥራ አጦች ሥራ እንዲፈጠርና የኑሮ ውድነትንና ለተገቢው ሥራም የሚመጥን ክፍያ/ደሞዝ እንዲኖር፣ የሚሉና ሌሎችም ከቆመላቸውና ከተዋደቀላቸው ዓላማዎቹ ውስጥ ነበሩ፣ ናቸውም።

ለነዚህ በርካታ ችግሮች መፍትሄ እንዲገኙላቸው መሠረቱንና ዕምነቱን በሕዝቡ ላይ ያደረገ፣ የጠላት አንጻራዊ "ጠንካራነት" ሳያስበረግገው የሕይወት እስትንፋሱ እስከትቆም ድረስ ለመታገል ቁርጠኝነት ያደረበት፣ ጽናትን የተላበሰ እንደ ኢሕአፓ የመሰለ ድርጅት መመሥረትና የበለጠ ተደራጅቶም መታገል ግድ ያለበት ወቅት ስለነበር፣ ለዚህ መልስ የተሰጠበት ክስተት ነበር ቢባል ሐቁን መናገር እንጂ ሌላ አይደለም። በወቅቱ የነበረውን የአገዛዝ ሥርዓት ለማስወገድ ለድል የሚያበቃው የትግል ሥልት ምን መሆን እንዳለበትም መልስ የሰጠበት ጭምር ነበር። ከተደራጀ ሕዝባዊ ትግል ውጭ ለችግሮቹ መፍትሄ ለማግኘትና ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥበት ሌላ አማራጭ የሆነ ፍቱን መድኃኒት እንደሌለም ያበሰረበት ነበር።

የአጼው አገዛዝ በኮለኔሉ፣ የኮለኔሉ ደግሞ በወያኔ አገዛዝ ተራ በተራ መተካትም ይህንን ሐቅ በምንም ዓይነት ሊሽረው ያልቻለ ክስተት ነው። ወደ ታሪክ ትቢያ የተጣሉት አገዛዞችና እነዚህኑ ተክቶ ያለው እንደነሱ ወደ ከርሰ መቃብሩ ለመሄድ እየተንደረደረ ያለውን የወያኔ ሥርዓት ጭምር በጥልቀት ስናጤናቸው፣ ኢሕአፓ የታገለላቸው ጥያቄዎች አሁንም ድረስ ገና ምላሽ ፈላጊ ሆነው እናገኛቸዋለን። የተለያዩ ዴሞክራሲያዊ ነክ የሆኑ መብቶች ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ተለቃቅመውና ኮፒ ተደርገው ወደ አማርኛ ተተርጉመው በወያኔ አገዛዝ ሰነድ ላይ ቢሰፍሩም የዜጎች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ መብቶች በተግባር አልተረጋገጡም። ሕዝብ መበደሉና መብት አልባ ለመኖር መገደዱ አሁንም እንደቀጠለ ነው። ዴሞክራሲ በልፈፋ ያለና ለወያኔ አገዛዝ የፖለቲካ ፍጆታ እንዲውል እየተደረገ ከመሆኑ ሌላ ለሕዝቡ የተረፈው ፋይዳ ጨርሶ የለም። ሀሳብን በነፃ ለመግለጽ መሞከር ዘብጢያ የሚያስወርድና በእስር የሚያስቀጣ ነው። ሕዝብ የሀገሩና የመሬቱ ባለቤት በመሆኑ ፈንታ ከቀዬውና እትብቱ ከተቀበረበት እየተፈናቀለ ለም የእርሻ መሬቱም ሆነ የከተማ ቦታ ለባዕዳን በርካሽ ዋጋ ይቸበቸብበታል። በሕዝባዊም (በሲቪሊም) ሆነ በፖለቲካ ማኅበር የመደራጀት መብቱ ተገፎ ለተለጣፊነትና ለጎሰኝነት የተመለመሉ ቡድኖች ከጫንቃው ላይ እንዲወጡ ተደርገው ባሕላዊ ዘፈን በማዘፈንና ዳንኪራ በማስረገጥ ማንነትህ ተረጋግጧል ተብሎ ይቀለድበታል። ተጨፈን እናሞኝህ በማለት እየተሳለቁበት ይገኛሉ። መሠረታዊ የሆነውን በውስጥ ጉዳይ የመወሰን መብቱን ግን በማናህሎኝነት ነጥቀውታል። የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጥያቄው በማንኛውም መልኩ ከጥንስሱ ጀምሮ ሂደቱ ተጠናቆ እስከሚወሰን ድረስ ጨርሶ ያልተካፈለበትን ውሳኔ ፈጻሚና አስፈጻሚ እንዲሆን አድርገውታል። በዚህም የተነሳ እየደረሱበት ያሉ እመቃዎች ከበፊቱ በተለያየና በከፋ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተደራራቢ ሁኔታዎች ቀጥለዋል። ይህ የሚያመላክተው አንድ ሐቅ ለሕዝብና ከሕዝብ ጋር የሚታገልና የሚያታግል የፖለቲካ ድርጅት የመኖር አስፈላጊነትን ነው። ለዚህም ነው ይህ ሁኔታ ሰፍኖ ሕዝብ መብት አልባ ኑሮ ለመኖር እስከተገደደ ድረስ ኢሕአፓ ከሕዝቡ ጎን በመሆን ትግሉን ለመቀጠል የሚገደደው።

አንድ ሕብረተሰብ ባለበት ቆሞ አይቀርምና፣ ጊዜ በሄደ መጠን ለውጥ መኖሩ የግዴታ ነውና፣ ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ባደረጋቸው ትግሎች የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ገና እልህ አስጨራሽ ጉዞዎችን መጓዝ ቢኖርበትም፣ ከሽንፈቱም ጭምር ተመክሮን እያካበተ ለመጨረሻው ድል ዋስትና የሚሆኑ በተግባርም እየተረጋገጡ ያሉ በቀላሉ የማይገመቱ ድሎችን መጎናፀፉ ደግሞ ሐቅ ነው። ዋና ዋናዎችን ለመጥቀስ ያህል -- ከሁሉ በፊትና ቅድሚያ የሚሰጠው የደርግ አገዛዝ በአባላቱና ደጋፊዎቹ (በድርጅቱ) ላይ ይህ ነው የማይባል ጥቃት ቢያደርስም፣ የወያኔ አገዛዝም በበኩሉ ተወስቶ የማያልቅ በደል የፈጸመበትና አሁንም እየፈፀመበት ያለ ቢሆንም፣ ኢሕአፓ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ፣ መከፈል የሚኖርበትን መስዋዕት እየከፈለ፣ ድርጅታዊ ሕልውናውን ጠብቆና አስጠብቆ፣ በሂደት የተሰባበሩ መዋቅሮቹን እንደገና በአዲስ አዋቅሮና ገንብቶ ትግሉን በፅናት ለመቀጠልና የሕዝብ አለኝታነቱን እስካሁን ድረስ በተግባር ለማረጋገጥ መቻሉ ነው። ይህ በበርካታ አባላቱና ደጋፊዎቹ መስዋዕት ክፍያ

የተገኘ ተመክሮ ወደፊትም ትግሉን ለማስቀጠል ዋስትና ሊሆን የሚያስችለው ጉዝጓዝ እየሆነ ያለው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም በትምህርት ሰጪነቱ ሊቆጠር የመቻሉ ሁኔታ ነው። ኢሕአፓ የትግል ዩኒቨርሲቲ ነው ተብሎ የሚጠራውም ይህና ከዚሁ ጋር በተያያዙ ክስተቶች እየተገኙ ያሉ ተመክሮዎችን በዋቢነትና ከግንዛቤ በመውሰድ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለም።

ሁለተኛ-- ሕዝብ ከታገለ አሸናፊ ሊሆን መቻሉ ብቻ ሳይሆን የትግሉን ውጤትና ድሉን ሊያስከብር ይቻለው ዘንድም ሕዝብ ራሱ እምነቱን ሊጥልበት የሚችል፤ ድጋፍና ተሳታፊነቱን የሚገልጽበትና የሚያረጋግጥበት፤ አቅጣጫ የሚያሲይዘውና የሚጠቁመው የፖለቲካ ድርጅትና የትግል ኃይል የማስፈልጉ ጉዳይ ከግንዛቤ መወሰዱ ነው። ይህም ብቻ አይደለም። የድርጅት ጥንካሬ ከሕዝብ የትግል መንፈስና መነሳሳት ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑም ይህንን መነሳሳት ለማዳበር የፖለቲካ ድርጅት ሚና ወሳኝና ከፍተኛ መሆኑ ከግንዛቤ መወሰዱ ሌላው የተገኘ ተመክሮ ነው።

ሶስተኛ-- የመደራጀትና የመታገል ጠቀሜታው በስፋት አመኔታ ማግኘቱ፤ ከዚህ ትግል አያሌ ተመክሮዎች በመቀሰሙ ለደርግም ሆነ ለወያኔ አገዛዝ እምቢኝ አሻፈረኝ ለማለት መቻሉ፤ ለሀገር አንድነት በዕኩልነት በጋራ መታገልና በብሔረሰብ አለመከፋፈል ጠቃሚነቱ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው። የድርጅትን ጠቃሚነትና ክብደት በሚከፈል መስዋዕት ብቻ ለመመዘን መጣር ስህተት መሆኑ፤ አርዓያነት፥ ጀግንነት ለትግል ቀስቃሽ አደራጅና አስተባባሪ መልካም እሴቶች መሆናቸው፤ ነፃነትን ያልተላበሰ፣ ሙብትን ያላስከበረ አስተዳደር ዞሮ ዞሮ አምባገነናዊነት የሚጠናወተው ክስተት መሆኑ እንዲሁ ከትግሉ ውጤቶች ውስጥ ናቸው። የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት አስፈላጊነትን በ1976 ዓ.ም. ባደረገው ጉባኤ ተቀብሎ ይህ አስተሳሰብ በሕዝብ ዘንድ ሰርፆ እንዲገባ ባካሄደው ተጋድሎ ተቀባይነት ማግኘቱና ለስኬታማነቱም የመለስ ዜናዊ አምባገነን አገዛዝ እንዳሻው እንዳይፈነጭ ሕዝብ እየታገለው መሆኑ ሁላችንም በገሃድ ያየነው ሐቅ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የብሔር ጥያቄ በመርህ ደረጃ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሙብት ማከበር ተገቢነቱንና ጠቃሚነቱን በማመን ሕዝባችን በእኩልነት የሚኖርባት ፌደራላዊት ኢትዮጵያን መመሥረት ተግባራዊ መፍትሄ ነው በማለት ያቀነቀነው አቋም ትክክለኛነቱ በሕዝቡ እየተረጋገጠ ለመምጣቱና የወያኔን በጎሳና ቋንቋ ላይ የተመሰረተውን አገዛዝ በመታገል ላይ መገኘቱ፤... ባጠቃላይ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉ በኢሕአፓ ግንባር ቀደምትነት ባለፉት ዓመታት በተደረጉ ትግሎች የተገኙ ተመክሮዎችና ውጤቶች ናቸው። በመሆኑም ኢሕአፓ እንደ ድርጅት የፖለቲካ ሥልጣን አልጨበጠም የሚለው አገላለጽ እስካሁን ሕዝቡ ከትግሉ ያገኛቸውን ውጤቶች ባዶ አርጎ በሌጣው የሚደረግ ድምዳሜ ነው።

የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው በሚል ቀመር ጠላትንና ወዳጅን ሳይለዩ ከማንኛውም ባዕድ ጋር እየተወዳጁ ብሔራዊ ጥቅምንና የሀገር ሉዐላዊነትን ለድርድር እያቀረቡ ከሥልጣን ለመውጣት መሞከር ስህተት መሆኑን የሚያመላክቱም ጭምር ናቸው። እነዚህና ሌሎችም ተመክሮዎች ከትግል ፅንሰ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ መስዋዕትነት ተከፍሎ የተገኙ ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘቡ ተገቢ ነው። ይህንን በመልካም እሴት የምንመለከተው ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ሥልጣን ለመውጣት ለሚያልሙ ሁሉ ከወዲሁ የማስጠንቀቂያ ደወል ቃጭል መሆኑን ሰምተው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ምክር ሰጪነቱንም እንዲገነዘቡ የምንቀሰቅስበት መሆኑ የማይታበል ነው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን የትግል ውጤቶች አስገኝቻለሁ ብሎ ደፍሮ የሚናገር ኢሕአፓ ብቻ ነው ብንል ሐቁን በታሪክነቱ ማስቀመጣችን እንጂ ሌላ ከቶ ሊሆን አይችልም። ኢሕአፓ ይህንን ውጤት በትግሉ በማስገኘቱ አባላቱና ደጋፊዎቹ በድርጅታቸው ይኮሩበታል እንጂ አይሸማቀቁበትም። ለወደፊቱ ትውልድ የሚነገር

በደማቸው የተፃፈ ታሪክ በመኖሩ ደስተኞች እንጂ የሚከፋቸው አይደሉም - በሕዝብም የተከበሩ የሚያደርጋቸው ይኸው ቀናና ጽኑ ትግላቸው ነውና።

በአሁኑ ወቅት በሰሜን አፍሪካ፣ ቱኒዚያ ተጀምሮ የተቀጣጠለው የለውጥ እሳት ከራሱ አልፎ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚገኙትን አጥለቅልቆ እስከ የመን ድረስ ዘልቆ በነዚህ ሀገራት የሚገኙ የአገዛዝ ክፍሎችን እየለበለበ፣ የተወሰኑ አምባገነኖችንም ከሥልጣን ባስወገደበት ወቅት፤ ሂደቱን በሚገባና በጥልቀት ባለመረዳት፣ የፖለቲካ ድርጅት ሚናን ለማሳነስ ከናካቴውም አያስፈልግም እየተባለ የሚቀነቀነው አስተሳሰብ ጠቃሚነቱ ለማን እንደሆነ ግልፅ ነው። የታጠቀና የተደራጀን አገዛዝ በግብታዊነት ማሸነፍ ይቻላል ተብሎ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ወያኔን ያስፈነድቀዋል እንጂ ከቶም የሚያስጨንቀው፤ እረፍት የሚያሳጣው፤ እንቅልፍ የሚነሳው ሁኔታ አይፈጥርበትም። ከዚህ እሳቤ በመነሳት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ የወያኔ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ሕዝብን በመስኩ፣ በተጨባጭ ከመቀስቀስ ይልቅ ወገቤን እያሉ መሆኑን ማየቱና መታዘቡ በርግጥም የሚያሳዝን ነው። እንደ ሰሜን አፍሪካው ሁሉ ተመሳሳይ ሁኔታ በሀገራችን በኢትዮጵያም ተከስቶ የወያኔ አገዛዝ ከሥረ መሠረቱ ተፈንቅሎ እንዲደመሰስ የሚያበቁ ከበርካታም በርካታ ምክንያቶች አሉ። ይህ ዕውነታ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ ሕዝብን ነጻነት የማጎናፀፍ ዓላማ አንግበናል የሚሉ የወያኔን ሥሥ ብልት ሊቆነጥጥ የሚችል፤ መሪዎቹን እንቅልፍ የሚነሳ የማደራጀት ተግባርና ሕዝብን ለትግል የሚያነሳሳ ቅስቀሳ ከማድረግ ይልቅ ሚዛን በማይደፉ ድርጊቶች መሰማራታቸው እየደረሰበት ካለው አሳዛኝና አሰቃቂ ሁኔታ ለመገላገል ከሚሻው ሕዝባችን አንፃር ሲገመገም አግራሞትን አስከትሏል። ይህም በድርጅት መሪዎች ላይ ሕዝብ ዕምነቱን እንዲቀንስ የተወሰነ አስተዋፅዖ ማበርከቱ ሊካድ የሚችል አይደለም።

ሕዝብን ከጭቆና አገዛዝ አላቆ ወደ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ አስተዳደር ለማሸጋገር ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለማድረግ በርግጥም ለሀገርና ለሕዝብ ፍላጎት መደራጀትን፣ በተግባር ማሳየትና በተግባር መፈተን ሁኔታው ከምንጊዜውም በላይ ጠያቂ በሆነበት በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ድርጅት ብቃት መለኪያ ይህ ዓይነት ሁኔታ ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? እየተባለ ከየቦታው የሚነገረውም አለምክንያት አይደለም። ተጨባጭ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ በተለይም እንዳሁኑ ደግሞ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የትግል ስልት መቀየስና መምራት አሁን ካልሆነ መቼ ሊሆን ይጠበቃል? የሚሉት ጥያቄዎች ምን ያህል በሕዝብ ላይ እምነቱን የሚጥል፤ ሕዝባዊ፣ ሀገር ወዳድ፣ ብዙሃኑን ሕዝብ በትግል ለማሳተፍ በፅናት የሚጥር የፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊነትን የሚያመላክት እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህንን ክፍተት ለመሙላት በኢሕአፓ በኩል ከምንጊዜውም በበለጠ በሚችለው ሁሉ ጥረት ለማድረግ ቆርጦ የተነሳ ሲሆን ይህንኑ እያደረገ ለመሆኑ ደግሞ በቅርቡ በተከታታይ ያደረጋቸው የቅስቀሳ ድርጊቶች የሚመሰክሩለት.ናቸው።

አንዳንድ የተቃዋሚ መሪ ነን የሚሉማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጋጣሚ ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ ግብታዊ እንቅስቃሴ ቢጀምር፤ ባልመሩት፣ ባላደራጁበት፣ ባልቀሰቀሱበት በአንዳንድ አገራት ውስጥ እንደታየው በባዕድ ድጋፍና እሹሩሩ ባይነት ከትግሉ አናት ላይ ለመቆናጠጥ በማለም በመለስ አገዛዝ ላይ የባዕዳንን ግፊትና እገዛን የሚያልሙ ብቻ ሳይሆን፣ አካሄዳቸው ይህንኑ የሚጠቁም ለመሆኑ በርካታ ፍንጮች ታይተዋል። መጨበጫ በሌለውና ለሚመጣው ማናቸውም ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ክፍል በማይገኝበት ለግብታዊ እንቅስቃሴ ቀጠሮና የመገናኛ ቦታ ሳይቀር በአደባባይ የሚሰጥ ጥሪ የዚሁ ነፀብራቅ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህንን በሚገባ የተገነዘበው ወያኔም በበኩሉ ይህንን ጥሪ እንዴት እየተጠቀመበት እንዳለ የሚያወጣቸውን የማፍረሻ መሳለቂያዎችን መመልከቱ ብቻ በቂ ነው። በርግጥም ከጥቂት ዓመታት በፊት የድርጅትን ክብርና የኢትዮጵያዊ ጨዋነትን የሚያስደፍር ትርኢት በመለስ ዜናዊ ዋና

አቀናባሪነት በቴሌቪዥን መስኮት እንዲታይ መድረጉን የምናስታውሰው ነው። ትርኢቱ በራሱና ይህን ትርኢት ተስታኮ የተለፈፈው ፕሮፓጋንዳ፣ ጤናማ አዕምሮ ያለው ማንኛውም ዜጋ ሊገነዘብ እንደሚችለው፣ የፖለቲካው ምህዳር ምንኛ አርቆ አስተዋይነት ያለው የፖለቲካ ድርጅትን አስፈላጊነት በግልፅ ያሳየበት ብቻ ሳይሆን ሕዝብ በስሙ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ምንነታቸውን በሚገባ ሊገነዘብ የቻለበት እንደነበር የፈጠጠ ሐቅ ነው ቢባል እውነቱን መናገር እንጂ ሌላ ከቶ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው ህዝብ እንመራሃለን የሚሉትን ግለሰቦችንም ሆነ ተቃዋሚ ነን ባዮችን በግብታዊነትና ስሜት ሳይሆን ረጋ ብሎ መፈተሽ፤ የሕዝብ ትግል ከግብ እንዲደርስ ከተፈለገ ባወጣ ያውጣው በሚል ቀመር ሳይሆን የድርጅትን ጉዳይ ደግሞ ደጋግሞ መግለፅና ማስረዳት የሚያሻው።

ተደጋግሞ እንደተገለፀው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከግቡ እንዲደርስ በተደራጀና በጠነከረ የፖለቲካ ድርጅት መመራትና መቀናጀት የሚገባው ለመሆኑ የፖለቲካን ሀሁን ለተገነዘበ ማንኛውም ዜጋ ሁሉ ግልፅ ነው። የድርጅት ጠባይ እንደ ወቅቱ ሁኔታ የሚቀያየር ሊሆን ብችልም እንዲሁም በሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ ከህዝብ ጋር ባለው ግንኙነት የሚገለጽ ቢሆንም በአሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅት ሲባል ለወያኔ ታማኝና ተለጣፊ የሆነ ሳይሆን ወዳጅና ጠላትን በሚገባ የተገነዘበና ድርጅታዊ ነፃነቱን ጠብቆና አስከብሮ ወያኔን ከነግሳንግሱ ለማስወገድ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ከማለት ውጪ ሌላ ትርጉም ሊኖረው ጨርሶ አይችልም። ላለፉት 20 አመታት ከሱ ጋር ለመለሳለስ የተደረጉ ጥረቶች በሙሉ ሕዝብን የታደጉ ሳይሆኑ ይበልጡኑ ለጉዳት የዳርጉ ናቸውና! ለዚህም ነው ውዳቂ የሆነ አስተሳሰብ ውድቀትን እንጂ እድገትን ሲያመነጭ በየትም ቦታ ታይቶ የማይታወቀው።

ወዳጅና ጠላት የመለየትን ጉዳይ አስመልክቶ በሰላማዊነትና በመቻቻል ሥም ለማጥላላትና ለማደብዘዝ ጥረት የሚያደርጉ፤ የወያኔን ልብ ለማራራት ውስጣዊ ፍላጎታቸው አሁንም እንደፀና ያሉ፤ ወያኔን ከሥልጣን ለማባረር ሳይሆን ዓላማቸው፣ የተወሰኑ ግለሰቦችን በማባረር አገዛዙን እንዳለ ለማስቀጠል መከራና ጣጣ ለመቀበል ዝግጁ ነን የሚሉና የሚያቅራሩ ባይጠፉም፣ መለስና የቅርብ ጓደኞቹ ግን የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን በሙሉ በጠላትነት ፈርጀውና መድበው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው እነዚህ ክፍሎች እንደተመኙት የሚቀየሩላቸው ሆነው አልተገኙም። እነዚህ ክፍሎች ወያኔ ገና ለሥልጣን ከመብቃቱ በፊት ዋናው የትግሉ መመሪያ የሆነውን የሁሉም ብሔረሰብን የመገንጠል ግዴታ አቋም ብሔራዊ ትግሉን ክፉኛ ሊጎዳ እንደቻለ ያልተረዱ ብቻ ሳይሆኑ አሁንም ከ20 ዓመት የሥልጣን ዘመኑ በኋላም በዚሁ ጥረታቸው እየቀጠሉበት በመገኘታቸው ከስህተታቸው ተገቢውን ትምህርት መቅሰም የሚገባቸው መሆኑ እየተናነቃቸው ይገኛሉ። በትግሉ ሂደት በደንቃራነት መሰለፍ ብቻ ሳይሆን የድሉን ጊዜ እንዲራዘም አስተዋፅዖ ማበርከታቸውም ሊሸሸግ የማይችል እውነታ ነው። ከዚህ በመነሳትም ነው ትግሉ በስኬታማነትና በድል እንዲጠናቀቅ ጠላትና ወዳጅን መለየት ወሳኝ የሚሆነው። ለዚህም ነው ወዳጅና ጠላትን የለየና በግልጽ የሕዝብንና የወያኔን ጎራ ለይቶ የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊነት የሚገለፀው።

ስለ ፖለቲካ ድርጅት ይዘት፤ ምንነትና ሚናን አስመልክቶ በርዕሱ ላይ ከሕብረተሰብ፤ ከሳይንስና ከሕግ አንፃር በስፋት ጥናታዊ ምርምርን ያካሄዱ ምሁራንና ሊቃውንቶች እንደሚከተለው ይገልጹታል።

የፖለቲካ ድርጅት የራሱ የሆነ አወቃቀርና የፖለቲካ መርሃ ግብር ያለውና የተወሰነ የጋራ እሳቤና ዓላማ ባላቸው አባላት የሚንቀሳቀስ፤ ሁኔታው ሲፈቅድም ፍትኃዊ በሆነ ሕዝባዊ ምርጫ ውስጥ ለመካፈል ጥረት በማድረግ እውቀትና ተመክሮ ያካባቱ አባላቱን በመንግሥት አስተዳደር ተቋማት ውስጥ ለሥልጣን እንዲበቁና በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚገኙ/ለሚከሰቱ ችግሮች፣ ድርጅቱ በሚያምንበትና በሚከተለው ራዕይ በመመርኮዝ መፍትሄ ይሆናል የሚሏቸውን

ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ በአንድነት የተደራጁበት ስብስብ ነው። ከዚህ አገላለጽ በመነሳት ሚናውን ስናጤን የፖለቲካ ድርጅት

1. ሕብረተሰቡን ከፖለቲካ ሥርዓቱ ጋር ማያያዝ፣ ማቆራኘት (የሚገለፀውም ሥርዓቱ ሕጋዊነት እንዲያገኝ ወይንም ደግሞ እንዲያጣ አስተዋፆ በማበርከት)፤
2. በሕዝብ አስተያየት ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፤
3. የሕዝብን የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ማዳበርና የደሞክራሲ ባህልን ማስፋፋት/መገንባት
4. በሕዝብ የፍላጎት ግንባታ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ፍላጎት መኖር፤ ለዚህም ያለመታከት ዜጎች በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ እንዲሳተፉ መጋበዝ መገፋፋት፡
5. ለአመራርነት ብቁ የሚሆኑ ዜጎችን ማዘጋጀትና መኮትኮት፤
6. ሁኔታው አመቺ ሆኖ ሲገኝ ፍትሃዊ፤ ነፃና ትክክለኛ በሆነ ህዝባዊ ምርጫ መካፈል፤
7. የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጎት በፖለቲካው ሥርዓት ምን እንደሆነ ማሳየት፤ የተወሰነ ውሳኔንም አግባብነት ያለው መሆን አለመሆኑን ኃላፊነትን ወስዶ ለህዝብ ማብራሪያ መስጠት፣ ማስረዳት፤
8. የተለያዩ የሕዝብ ጎራ ጥቅሞች ሊቻቻሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

የሚሉት ሚናዎቹ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከነዚህ ከተዘረዘሩት የድርጅት ሚናዎች በመነሳት ስለፖለቲካ ድርጅት ሲወሳ በሀገራችን በሰፈነው ባሁኑ የፖለቲካ ሁኔታ ሊሰጥ የሚገባው ግንዛቤ፤ ሕዝቡ ነፃነቱን እንዲጎናፀፍና የራሱን ጉዳይ በራሱ እንዲወስን ብሎም ለመሠረታዊ ጥያቄዎቹ መፍትሄ ለመስጠት ማስቻልን ዓላማ አድርጎ የነደፈውን የፖለቲካ መርሃ ግብር በሕዝባዊ ይሁንታ ተግባራዊ ለማድረግ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚታገል ማለት ነው። ይህንን መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ከሕዝቡ ጋር የቀን ተቀን እንቅስቃሴውን በማቀናበር፤ የሕዝቡን ችግር በፖለቲካ መነጽር እያየ የመፍትሄ ሃሳቦችንም በሕዝብ ፍላጎት ላይ መሥርቶ፤ የሕዝብ አስተያየት በአገዛዙ ላይ የበላይነት እንዲጎናፀፉ ለማስቻል የሚንቀሳቀስ ማለት ነው።

የፖለቲካ ድርጅት ለሥልጣን መታገሉ በነጠላው ቢወሰድ ችግር እንዳልሆነ በተደጋጋሚ የተገለፀ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ማንኛውም ድርጅት የሕዝብን ባለሥልጣንነት በተግባር ተፃርሮ፣ አግባብነት በሌለው መንገድ እራሱን ከሥልጣን ለማውጣት ሲንቀሳቀስ፤ ድርጅቱ የሕዝብ ትግል መሣሪያ፣ ለሕዝብ ችግር መፍትሄ ፈላጊ በመሆን ፈንታ፣ ሕዝብን ተክቶ የሕዝብን ሥልጣን በእጁ ለማስገባት የሞከረ፤ ለሕዝብ ትግል ጠቃሚ መሆኑ ቀርቶ መሰሪነትና ተንኮለኛነት የተጠናወተው የችግሩ አካል ሆኖ ይፈጠማል። ይህ እንዳይሆን ሕዝብ ከዚህ ዓይነት ድርጅት ራሱን በማራቅ ድጋፉን በመንሳት፣ እርባነቢስ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት የሚጠበቅበትም በዚሁ ምክንያት እንጂ የዴሞክራሲ መብትን ለመፃረር እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በመሆኑም፣ ታግያለሁና ሥልጣን ይገባኛል የሚል አባዜ የተጠናወተውን በሙሉ፤ ሕዝብ መቼ ታገልልኝ ብዬ ውክልና ሰጠሁህ ብሎ መጠየቅና ውክልና ሰጭነቱ ከእጁ እንዳይወጣ አጥብቆ መታገል የሚጠበቅበት ይሆናል - በዚህም ነው ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ድርጅቶች ማንነታቸውና ይዘታቸው የሚፈተንበት።

በሀገራችን ባሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ድርጅትን ስናስብ፣ ሕዝብ ለጉዳት እንዳይዳረግ የወያኔን የአፈና መረብ ሥልታዊ በሆነ መንገድ በመቋቋም፤ ከአጉል ግፍጫም ራሱን በማራቅ፤ የሕዝብን ትንሳኤ የሚፈልጉትን ሁሉ፣ ትግሉ መሠረታዊ ለውጥ በሚያስገኝ ሁኔታ እንዲካሄድ ተግባራዊ አደረጃጀትን የሚሰጥ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው። የወያኔ ሕገ አገዛዝን ሕጋዊነት የማይቀበል፤ ለወያኔ የበላይነት ተገዶ ማጎብደድን፤ ጫማው ሥር መነጠፍን የሚጠየፍ፤ የወያኔን ሕግ

በማክበር ሰብዓዊነትን ለውርደት የሚዳርግን ሂደት ሁሉ የሚቃወም ማለት ነው። በምክር ቤት ተብዬ በሰበሰባቸው ደጋፊዎቹ ያስወሰናቸውና በተለያዩ ሰነዶች ያስቀመጣቸውን፤ ራሱ እንኳ የማያከብራቸውን ሕገ ወጥ አሰራሮች በሙሉ ሰጥ ለጥ ብሎ መቀበልን የሚቃወም ብቻ ሳይሆን ጨርሶውኑ መጣስ ሀገራዊ ግዴታው መሆኑን የተገነዘበ ማለት ነው።

አንድ የፖለቲካ ድርጅት በሀገራችን፣ ባለፉት 20 አመታት ባካሄዳቸው እርኩስ ተግባራቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተጠላው ወያኔን ይበልጥ በመነጠል ለማድከም፤ በግልፅም በስውርም የሚረዱትን ክፍሎችና ግለሰቦችን ባዕዳንን ጨምሮ ከሱ እንዲገለሉና እንዲርቁ ለማድረግ፤ በአንፃሩ የሕዝብ ጎራን በማስፋት፤ ወዳጅና አጋሮቹን በማበራከት፤ በተለያዩ ጥያቄዎች ዙሪያ ሊሰባሰብ የሚችለውን ሁሉ በማሰባሰብ ለሕዝባዊ ትግሉ ዋስትና መሆናቸውን ተገንዝቦ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጥር መሆኑ የሚጠበቅ ነው። እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ አርቆ አስተዋይነትና የፖለቲካ ብስለት፣ ብልህነትን፣ ከራሱ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መሰል የፖለቲካና ማህበራዊ ችግሮች ካላቸው ሀገሮች ከተደረጉ እንቅስቃሴዎች ድሎችና ሽንፈቶች ተመክሮ ለማግኘት የሚጥር የፖለቲካ ድርጅት መሆን መቻል አለበት። ባጭሩ ራሱን በተወሰነ እውቀት ብቻ ገድቦ የማይንቀሳቀስ ለሕዝብ ታዳጊ ለመሆን የሚጥር ማለት ነው። ውስጣዊ ድክመትንና ችግርንም አስመልክቶ በሚመለከታቸው አባላቱ መፍታት ሲገባ ለጠላት መጠቀሚያ፤ መሳቂያና መሳለቂያ ከመሆን ራሱን የሚከላከል፡ ተጠያቂነቱን ለሕዝብ ብቻ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ማለት ነው። በየጊዜው በሚደረግ የርስ በርስ ሽኩቻና መጠላለፍ በሕዝብ ዘንድ ሊገኝ የሚችል አመኔታን ከሚያሳጣና ለወያኔ መልካም እድል ከሚፈጥሩ ተግባራት ራሱን የሚቆጥብ መሆን ይኖርበታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሕብረት መኖር ጠቃሚነቱ የማይታበል ቢሆንም ሕብረት ፈላጊና ጠሪ እየመሰሉ ግና በተግባር ሀቀኛ የትብብር ጥሪን እያኮላሹ ካሉ ክፍሎች ራሱን የሚጠብቅና ሕዝብንም ከእንደነዚህ ዓይነት መሰሪ ተንኮለኞች የሚከላከል ማለት ነው።

ተፈላጊው የፖለቲካ ድርጅት ስንልም የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሮቹና ብሶቶቹ ከደሙና ከሥጋው የተዋሃዱ፣ ከልቡ የሰረጹ፣ የሕዝቡን የልብ ትርታ እያዳመጠ ለጥፋት የሚዳርጉትን መንገዶች የሚከላከል፤ አንድነቱን የሚጠብቅ፤ ኃይሉን የሚያጠናክር፤ ለዚህም በብቃት የመደራጀት አስፈላጊነትን አንግቦ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ ማለት ነው። ከሕዝብ ጋር የሚያስተሳስረውን የታሪክ ሰንሰለት የሚንከባከብ፤ መልካም እሴቶቹን የሚያከብር የሕዝብ አለኝታ ለመሆን በዚህም የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት የሚንቀሳቀስ ማለት ነው። ሐቀኛ ትግል በሕዝብ ተሳትፎ የተደገፈ፣ በሕዝባዊ ዓላማ ላይ የቆመ ሕዝባዊ ትግል የሚል ትርጉም ያለው ነውና፤ ጥቂቶች ብቻ በእኛ የበላይነት የሚል ትግል አካሂደው ነፃነትንና መብትን ለሕዝብ ማጎናፀፍ ስለማይቻል (ወያኔም ጉልህ ምሳሌ ነውና) በትግሉ የሕዝቡን ግንባር ቀደም ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚንቀሳቀስም መሆን አለበት። የፖለቲካ ድርጅት አመፅ እንዲነሳሳ መቀስቀስ ብቻ ሳይሆን አመፁ ከተነሳ የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ሳይመለሱ አመፁ ማቆም እንደሌለበት ተግቶ የሚታገልና የሚያታግል መሆኑ ግድ ይላል። ... ሌላም፤ ሌላም።

እነዚህ ከላይ በጥቂቱ የተገለጹትና የአንድን ታጋይ የፖለቲካ ድርጅት ጠባይ ባጠቃላይ በኛም ሀገር በተለይ ያለውን የሚገልጹ ነጥቦችን የሚረዳና የተረዳ በርግጥም ሕዝብን ለማነሳሳት የሚያስችሉ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ይገነዘባልና ተገቢውን የትግል ስልት ነድፎ ለመንቀሳቀስ የማንንም ጉትጎታ የሚፈልግ እንዳልሆነ ግልፅ ነበር። ከኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበቱ ጀምሮ የነፃነት እጦት፤ የበደሎች ክፋትና መብዛት፤ ቅጥ ያጣ ሙስና መስፋፋት፤ የሀገር ሕልውና በመለስ አገዛዝ እንዳሻው መረገጥ፤ ለም የእርሻ መሬት በርካሽ ለባዕዳን መቸርቸርና የገበሬዎች ከቄያቸው መፈናቀል፤ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መበራከት፤ የመልካም አስተዳደር እጦትና የፍርድ ጉድለት፤ የሥራ አጥነት በተለይ በወጣቱ ላይ መብዛት፤ የሀገርና የሰብዓዊ ክብር መረገጥ፤ ቱባ ቱባዎቹ ብቻ ሳይሆኑ የበታች

ባለሥልጣናት ጭምር በሥልጣን መባለግ፤ የኑሮ ዋስትና አለመኖር፤ በቂ የትግል ማነሳሻና መቀስቀሻ ሊሆኗቸውም በቻሉ ነበር። ታዲያ እነኝህን የሕዝብ ብሶቶች ከግምት በማስገባት በቅርቡ የተቀጣጠለውና አካባቢውን እየንበኘ ያለው የለውጥ እሳት በሀገራችን ለሚገኙ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶች ሕዝባችንን ለመቀስቀስ ራሳቸውን፣ የድርጅታቸውን ጥንካሬና ድክመት መርምሮ መፍትሄ ጭምር ለማፈላለግ አጋጣሚው በጠቀማቸው ነበር። ባለፉት የትግል ዓመታት፣ በተለይም በተደጋጋሚ በወያኔ የበላይነትና አመራር በተካሄዱት ምርጫ ተብዬ ተውኔቶች ተካፋይ ከነበሩት ድርጅቶች ውድቀት ከተገኙ ተመክሮዎች በመገንዘብ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ በሀገራችን ሁኔታ ትግሉ ምን መሆን አለበት የሚለውን አስመልክቶ ሰፍኖ የነበረው ብዥታ ጠርቷል የሚል ግምት ያለ ቢመስልም አሁንም አብዛኛው በግብታዊነት ላይ እምነታቸውን የጣሉ በመሆኑ ወቅቱን ጠብቆ በወያኔው የበላይነት ለሚጠናቀቅ የምርጫ ቲይትር ጠባቂ መሆናቸውን እንገነዘባለን።

በመሆኑም ሕዝባችን ምን ጊዜም ቢሆን የወደፊት እድሉን የመወሰን እጣ ለእንነደዚህ ዓይነት ድርጅቶች ጨርሶ መተው የለበትም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉንም ድርጅቶች ባስገረመና ባስደነቀ ደረጃ ከድርጅቶች ቀድሞ ነቅቶና ለትግል ተነሳስቶ መልካም ውጤቶችን በማስመዝገቡ ትምህርት ገብይቶበታልና ይህንን በፍፁም ሊረሳው አይገባም። በዚህ ወቅት ከጎኑ የቆሙትን ድርጅቶች አቅፎ ደግፎ በመገኘት ሊያነሳ የሚችለው መልዕክት፤ ወቅቱን በሚገባ ተገንዝባችሁ በመልፈስፈስ ሳይሆን በመራራ ትግል፤ ፍርሃትን ባስወገደ ቆራጥ ትግል አደራጁኝ፤ አቅጣጫ ስጡኝ የሚል ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለታጋዮች እየሰጠ ያለው መልዕክት ሁኔታው ያቀረበላቸውን አጋጣሚ ተጠቅመው ከሕዝብ ከራሱ ጋር ለመሰለፍ ወገባቸው የሚደከምባቸው፤ ቀሚሳቸው የሚያደናቅፋቸው ሁሉ ከመዳመጣቸው በፊት ሰልፋቸውን እንዲያሳምሩ ብቻ ነው። ይህም ተጨባጭ ብሔራዊና አካባቢያዊ ሁኔታን ያገናዘበ የትግል ሥልት ቀይሳችሁ ለወሳኙ ፍልሚያ ከጎኔ ተሰለፉ የሚል የሕዝብ ጥሪ እንጂ ሌላ አለመሆኑን የሚያስገነዝብ መልዕክት ነው። የኢሕአፓም የ39 ዓመት የትግል ተመክሮ ዋና መልዕክት ከዚህ ሌላ አይደለም።

የድል ዋስትና የፖለቲካ አመራር ብቃትና ጥንካሬ ነው!!!
የፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊነትን ማደብዘዝ ይቁም!!
እናቸንፋለን !!!